# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ታኅሣሥ 28 ቀን 2004 ዓ.ም**

**በአዳማ ዩኒቨርስቲ ከፍተኛ ግጭት ተከሰተ፤**

**በሆሳዕና ከተማ ከዩኒቨርስቲ ተመርቀው ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶች በፖሊስ ተደበደቡ፤**

**የፖሊስ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር የሆነው ጄኔራል ከስራው ሊሰናበት መሆኑ ተጋለጠ፤**

**የፍትህ ጋዜጣ አዘጋጆች የድረሱልን ጥሪ አሰሙ፤**

የወያኔ ቡድን ለከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲው እንዲያመቸው በዘረጋው አገዛዝ ምክንያት ለዘመናት ተፋቅሮና ተግባብቶ የኖረውን ህዝብ በብሔር እንዲቡዋደን በማድረጉ ግጭቶች ከግዜ ወደ ግዜ በየቦታው እየተከሰቱ መሆኑን ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሰን ጥቆማ አጋለጠ፡፡

በተለይ ከቅርብ አመታት ወዲህ ወያኔ በፈበረካቸው ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ሊማሩ በሚገቡ ተማሪዎች መሀከል ከፍተኛ ግጭት እየተፈጠረ እስከ መገዳደል ከመድረሳቸውም በተጨማሪ የሀገሪቱን ባህልና ወግ ብሎም ማንነት ሊያበላሽ በሚችል መልኩ ቡድንተኝነት እየተስፋፋ መምጣቱን ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ሰሞኑንም በአዳማ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በብሔር ልዩነት ግጭት ተከስቶ በርካታ ተማሪዎች ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ እስከ ዛሬ ድረስ ትምህርት ተቁዋርጦ እንደሚገኝ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

ወያኔ ለአገዛዙ እድሜ ማራዘሚያ ይሆነኛል ብሎ የዘረጋው ይሄው የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ተልዕኮ በተሰጣቸው ጥቂት ተማሪዎች አማካኝነት ብጥብጥ እና ሁከት እንዲነሳ አድርገው ተማሪዎች በፌዴራል ፖሊስ እና በኦሮሚያ ፈጥኖ ደራሾች ድብደባና እንግልት

እንዲደርስባቸው ከመደረጉም በተጨማሪ ከ20 በላይ የሆኑት ተማሪዎች ላይ የከፋ ጉዳት እንደደረሰባቸውም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል፡፡

ታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ.ም ረፋዱ ላይ በአዳማ ዩኒቨርስቲ ቲሌቪዥን መመልከቻ አዳራሽ ውስጥ በተከሰተው በዚሁ ብሔር ተኮር ግጭት ላይ ዋነኛ ተዋናይ የነበሩት የወያኔ አባል የሆኑ የ3ኛ ዓመት ተማሪዎች አንዱን ብሔር ከሌላው ጋር እያወዳደሩና እያንቋሸሹ በመደመጡ ተማሪው እርስ በርስ ከመጣላታቸውም በተጨማሪ በግቢው ውስጥ በድንጋይና በዱላ ሲፋለሙ እንደነበርም የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል፡፡

ዛሬ ወያኔ በህዝብ እና በሀገር ላይ የሚፈጽመውን በደልና ጥፋት በጋራ ሆነው እንዳይታገሉ ለማድረግ በነመለስና በረከት ትዕዛዝ የሚሰጣቸው እነዚሁ የወያኔ አባል የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በያሉበት ካምፓስ ግዜ ጠብቆ በሚፈነዳ የእርስ በርስ ግጭት እየሞሉ በተማሪዎች መሀከል መግባባት እና አንድነት እንዳይኖር ከማድረጋቸውም በላይ ብጥብጥ እንዲነሳ እያደረጉ መሆኑን ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የሚደርሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

የአዳማው ዩኒቨርስቲ ሁከት መነሻ የሆነው የወያኔ አባል የሆኑ የ3ኛ ዓመት ተማሪዎች በቲሌቪዥን የሚሰራጨውን የወያኔ ባዶ ቅስቀሳ እያወደሱ ባለበት ግዜ ሌሎች ተቃውመው ከአዳራሹ ሊወጡ ሲሉ እነዚሁ ጭር ሲል አንወድም የሚሉት የወያኔ ተላላኪ ተማሪዎች እንዴት ልማት ሲሰራ አትደግፉም በማለት ፀብ ከመፍጠራቸውም በተጨማሪ ግጭቱን ወደ ብሔር በመቀየራቸው ከፍተኛ ችግር ሊፈጠር እንደቻለም ዘገባው ገልፆዋል፡፡

የችግሩ መንስኤና ዋና ጠንሳሽ የሆኑት የወያኔ አባል ተማሪዎች በፌዴራል ፖሊስ እና በኦሮሚያ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶች ሽፋንና ከለላ ሲደረግላቸው በሌሎቹ ላይ ግን ይህ ቀረሽ የማይባል ድብደባ እንደተፈፀመባቸውና በተለይ በ20 ተማሪዎች ላይ ወንዶቹን ብልታቸውን ሴቶቹን ደግሞ ማህፀናቸውን በመርገጥ ሲያሰቃዩዋቸው እንደነበረ ከዩኒቨርስቲው አከባቢ የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል፡፡

ይሄው ግጭት ከተከሰተበት ከሐሙስ ታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 28 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ትምህርት ያልተጀመረ ከመሆኑም በተጨማሪ ተማሪዎች በፍርሀት እና በድንጋጤ ግቢውን ጥለው ወደ የቤተሰቦቻቸው ለመሄድ መገደዳቸውን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ያስረዳል፡፡

ዛሬ የወያኔ ቡድን በጎጥ በሚል ገበሬውን አምስት አምስት በመመደብ ለቁጥጥር እንዲያመቸው ከማድረጉም በላይ ወደ ከተማም ሆነ ወደ ፈለገው መንገድ እንዳይሄድ የቅርብ ቁጥጥር እና ክትትል እየተደረገበት እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ገበሬው ታፍኖ በሚገኝበት ወቅት ልጆቼ ተምረው ያሳልፉልኛል ብሎ ላቡን አንጠፍጥፎ ወደ ዩኒቨርስቲ ቢልካቸውም ምላሹ ግን በዘር እንዲበታተኑና ትምህርታችን አቋዋሩጠው ወደ ቀዬአቸው እንዲመለሱ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በቂቱ ዩኒቨርስቲ እና በጅማ ዩኒቨርስቲ ውስጥም ከዚህ ቀደም ተማሪዎቹን እርስ በርስ በብሔር በመከፋፈል ግጭት እንዲቀሰቀስ በመደረጉ ቁጥራቸው የበዛ ተማሪዎች ለከፍተኛ ጉዳት የተዳረጉ ሲሆን በተለይ በቂቱ ሁለት ተማሪዎች በዚሁ ሳቢያ መሞታቸው ይታወሳል፡፡

ከአንድ ወር በፊት በተመሳሳይ በአለማያ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በተማሪዎች መሀከል ብጥብጥ እንዲከሰት ተደርጎ ሶስት ተማሪዎች በስለት ተወግተው ከፍተኛ አደጋ ደርሶባቸው ድሬዳዋ ሆስፒታል እንዲገቡ የተደረገ መሆኑን ያስታወሰው የደረሰን ዘገባ በወቅቱ የወያኔ አባል የሆኑ መምህራኖች ግጭቱ እንዲከሰት የሰሩት ተንኮል እንደነበረም ዘገባው አስታውሶዋል::

በሌሎች ወያኔ በቀፈቀፋቸው ዩኒቨርስቲ ተብዬ ውስጥም ተመሳሳይ ችግሮች እየተከሰቱ በተማሪዎች ላይ አደጋ እየደረሰባቸው ለህክምና ወደ ጳውሎስ ሆስፒታል እየተላኩ እንደሚመጡና አንዳንዶቹ ሲሻላቸው ጥቂቶቹ ደግሞ ለአካለ ጎዶሎነት ተዳርገው ትምህርታቸውን አቋዋረጠው የተቀመጡ ተማሪዎችም መኖራቸው ይታወቃል::

ዛሬ የወያኔ ቡድን አዛዥ ናዛዥ የሆኑት ሁለቱ በተለይ መለስ ዜናዊ እና በረከት ስምኦን መላ የሀገሪቱን ህዝቦች በደህንነት አፍነው ከመያዛቸው በተጨማሪ በየግዜው ወደ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚገቡትን ተማሪዎች በግዴታ አባል እንዲሆኑ በማስገደድ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ተማሪዎች በአባልነት ቢታቀፉም የወያኔን ፖለቲካ ፍጹም እንደማይደግፉ በማወቃቸው አሁን በይበልጥ ወደ ገበሬው ፊታቸውን ማዞራቸውም ታውቆዋል::

ምንም እንኳዋን የተማሪዎች ድጋፍ አጠራጣሪ ነው ቢባልም ጥቂት የሆኑት ግን የወያኔን የከፋፍለህ እና የበታትነህ ግዛ ፖሊሲ ደጋፊ በመሆን በተማሪዎቹ መሀከል ሰላም ጠፍቶ ብጥብጥ......ፍቅር ጠፍቶ ጥላቻ እንዲነግስ ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ እንደሚገኙም ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የሚደርሱን ጥቆማዎች ያስረዳሉ::

ወያኔ ባህልን አጉዳፊ...... ሀገርን በታኝ ከመሆኑም በላይ አዲሱ ትውልድ ባህሉንና ወጉን እንዲሁም ማንነቱን ጠብቆና አክብሮ እንዳያድግ ሆን ብሎ ዘመን አመጣሽ የውጭ ሀገር ብልሹ ተግባራትን እንዲወርሱ እያደረገ ዛሬ በዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በአቅራቢያቸው በሚገኝ ከተማ ውስጥ በየምሽቱ ጭፈራ ቤት ግዜያቸውን እያሳለፉ ሲሆን ወንድ ተማሪዎችም በሀሺሽ እና በጫት ሱስ ተጠምደው ስለ ሀገር ቀርቶ ስለራሳቸው እንዳያስቡና የተንጋደደ ዜጋ ሆነው እንዲቀሩ እያደረገ ይገኛል::

በተለይ በአዋሳ፤በጅማ፤በጅጅጋ፤በድሬዳዋ እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚማሩ ወጣቶች ከትምህርታቸው ይልቅ ለሌላ ለርካሽ እና ባህል አጉዳፊ ተግባራት የተዳረጉ በመሆኑ ሴቶች በየምሽት ክለቡ እየዞሩ ሲዝናኑ ወንዶች ደግሞ ባገኙት አጋጣሚ ሆኑ ለጥፋት ተሰማርተው እንደሚገኙም በቀርቡ የተደረገ ጥናት አመልክቶዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ተምረው የተመረቁ ወጣቶች ስራ አጥ ሆነው ለቤተሰቦቻቸው ሸክም ከመሆናቸውም በላይ ለጎዳና ህይወት በመዳርጋቸው በየአካባቢው የተቃውሞ ድምጽ ማሰማት መጀመራቸው ታወቀ::

በደቡብ ክልል ውስጥ በሀዲያ ዞን ዋና ከተማ በሆነችው ሆሳዕና ነዋሪ የሆኑ ከዩኒቨርስቲ ተመራቂ ስራአጥ ወጣቶች ስራ እንዲሰጣቸው ለአካባቢው ባለስልጣናት በተደጋጋሚ ግዜ አቤቱታ ቢያቀርቡም ሰሚ ባለማግኘታቸው ሰሞኑን የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጋቸው ታወቀ::

ስራ አጥ ወጣቶቹ ሰሞኑን ለዞኑ ከፍተኛ ባለስልጣን ለሆነው ዋና አስተዳዳሪ ስራ ይሰጠን ብለው ጥያቄ በማቅረባቸው በፖሊስ ድብደባ የደረሰባቸው መሆኑንም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል፡፡

ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ተምረውና ተመርቀው 2 ዓመት እና ከዚያም በላይ ስራ አጥ ሆነው በከተማዋ የቆዩ ከ500 በላይ የሆኑ ወጣቶች ስራ ይሰጠን ብለው ተቃውሞ ሰልፍ በማሰማታቸው ህዝቡን ለአመጽ ልታነሳሱ ነው በሚል ከፍተኛ ድብደባ እንደተፈጸመባቸው ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

ሐሙስ ታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ.ም ስራ አጥተው ለጎዳና ህይወት የተዳረጉት እነዚሁ ወጣቶች ስራ እንዲፈለግላቸውና እንዲሰጣቸው ጥያቄ አዘል ተቃውሞ በማሰማት ላይ እንዳሉ በከተማዋ ሰፍሮ ባለው የፌዴራል ፖሊስ ተከብበው በቆመጥ እንዲደበደቡ ከመደረጋቸውም በላይ አስተባባሪ ናቸው የተባሉ 10 ወጣቶችን ነጥለው ለእስር እንደዳረጉዋቸው ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

በወቅቱ 10 አስተባባሪ ናቸው የተባሉ ጉዋደኞቻቸው ከመሀከላቸው መወሰዳቸውን የተመለከቱት ተቃውሞ አቅራቢ ወጣቶቹ በብስጭት ልቀቁዋቸው ብለው ከፖሊስ ጋር ግብግብ በመፍጠራቸው ሁለት ፖሊሶች የመፈንከት አደጋ ሲደርስባቸው ሌሎችም በድንጋይ እንደተወገሩ ከአይን እማኞች የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

በሆሳዕና ከተማ በተደረገው በዚሁ ፍልሚያ የከተማዋ ወጣቶችም እገዛ እንዳደረጉላቸውና የነሱ ጥያቄ የእኛም የነገ እጣ ፈንታ ነው በማለት ቁጣቸውን ከመግለፃቸውም በተጨማሪ ፖሊሶቹን እያራወጡ ጥቃት እንደሰነዘሩባቸው የገለፁት የአይን እማኞቹ የፌዴራል ፖሊሶቹ ወደ ካምፓቸው በመግባት መሳሪያ ታጥቀው እንደተመለሱና ወጣቶቹ ላይ በሰደፍ ድብደባ እንደፈጸሙባቸውም እነዚሁ የአይን እማኞች አስረድተዋል፡፡

በዚሁ በተፈጠረው በጥብጥ እና ግጭት ሳቢያ በከተማዋ ያሉ ትምህርት ቤቶች ለሁለት ቀናት ትምህርት ተቁዋርጦ እንደነበረ የገለፁት የአይን እማኞቹ በአሁኑ ሰዓትም በከተማዋ ውስጥ ፍርሀት ነግሶ እንደሚገኝም አክለው ገልፀዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በሆሳዕና ከተማ እንደተከሰተው ተቃውሞ በይፋ አይሁን እንጂ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎችም ተበትነው የተቀመጡ ምሩቃን ወጣቶች ውስጥ ውስጡን ተቃውሞ ከማሰማት አልፈው በአቅራቢያቸው ካሉ ካድሬዎች ጋር ግጭት እየፈጠሩ እንደሚገኝም የሚደረሰን ጥቆማ ያብራራል፡፡

በሌላ ዜና የወያኔን ቡድን ለ20 ዓመታት ሲያገለግል የነበረው የፖሊስ ጄኔራል መኮንን በግዳጅ የእረፍት ፍቃድ ሞልቶ እንዲወጣና ሲመለስም ከስራ ሊሰናበት እንደሆነ የፌዴራል ፖሊስ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ፡፡

ዶክተር ጄኔራል ሀብታሙ የተባለው ይሄው መኮንን ከ70ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በፖሊስ ሆስፒታል በህክምና ሙያ ሲያገለግል የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ከወያኔው ባለስልጣን ሀሰን ሽፋ ጋር መግባባት ባለመቻሉ እና ግጭቱ ሊከሰት እንደቻለ የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮች በተለይ ለህክምና ለሚመጡ የፖሊስ አባሎች የሚደረገው አቀባበል አናሳ በመሆኑ ሊስተካከል ይገባል በሚል

ሙግት ሲገጥም እንደነበርና በዚህና በሌሎች ምክንያቶች ከስራ ሊሰናበት እንደሚችል ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

የፖሊስ ሆስፒታል ሀኪም ሆኖ ከ30 ዓመት በላይ ሲሰራ የነበረው ጄኔራል ዶክተር ሀብታሙ በግዴታ የእረፍት ፎርም ሞልቶ እንዲወጣ በሀሰን ሽፋ ትዕዛዝ የተሰጠው ቢሆንም በቅርቡ በመከላከያ ውስጥ በተደረገው የነባር መኮንኖች ምንጠራ አንዱ አካል ሳይሆን እንዳልቀረም ምንጮቹ ግምታቸውን ያሰፍራሉ፡፡

የፖሊስ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር የነበረው ዶክተር ሀብታሙን ጨምሮ ሌሎች የህክምና ባለሙያ የሆኑ መኮንኖች የስንብቱ አካል ሊሆኑ እንደሚችል የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ ለረዥም ዓመታት በላብራቶሪ ስራ ውስጥ ሲሰሩ የነበሩት ዋነኛ ተጠቃሽ ናቸው ሲሉም ገልፀዋል፡፡

መተካካት በሚል አዲስ የማባረሪያ ስልት የተጀመረው የነባር መኮንኖች ምንጠራ ወደ ፖሊሶችም እንደሚዘልቅና እንደሚስፋፋ የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ በሆስፒታል ውስጥ በሚሰሩ ነባር መኮንኖች ላይ እንደሚያይልና በምትካቸውም የህወሀት አባል የሆኑ ወጣቶች ሊሰገሰጉ በዝግጅት ላይ እንደሆኑም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

የመከላከያ ነባር መኮንኖች ከስራ ከተሰናበቱ በሁዋላ ችግር እንዳይፈጥሩ በሚል በገንዘብና በሌሎች ጥቅማጥቅሞች እየተያዙ ቢሆንም በእነሱ ቦታ የአድዋ ተወላጅ የሆኑት አፍለኛ ወያኔዎች እየተተኩ መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በፖሊሶቹም ምትክ በተመሳሳይ እንደ መከላከያዎቹ ሊተኩ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

በመጨረሻም በነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች ላይ የሚደርሰው አፈና እና እንግልት በስፋት ቀጥሎ እንዳለ የፍትህ ጋዜጣ አዘጋጆች ሰሞኑን ገለፁ፡፡ ህዝብ የማወቅ መብት አለው ብለው በመስራት ላይ የሚገኙትን የነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች የወያኔ ቡድን እያስፈራራና እያዋከበ ከመሆኑም በተጨማሪ በይፋ በአደባባይ መደበደብ እንደጀመረም ታወቀ፡፡

ሰሞኑን የፍትህ ጋዜጣ አዘጋጆች በደህንነት ክትትል ስር እንደሆኑና አንደኛው የዝግጅት ክፍሉ ባልደረባ እና አሳታሚ የሆነውን ጋዜጠኛ ማስተዋል ብርሀኑ የደህንነት ኃይሎች ደብድበው መታወቂያ እስከ መቀማት ከመድረሳቸውም ሌላ በቢሮዋቸው ውስጥ እንዲውሉና እንዲያድሩ መገደዳቸውን ለህዝብ ይፋ አድርገዋል፡፡

ለይስሙላ የጋዜጠኞችን መብት አከብራለሁ እያለ በህዝብ ላይ የሚሳለቀው የወያኔ ቡድን ባሳለፍነው ወር ብቻ ሶስት ጋዜጠኞች ከሀገር እንዲሰደዱ ማድረጉና ይህም አልበቃ ብሎ ባሉት ጥቂት ጋዜጠኞች ላይ ጥቃት መሰንዘሩ እጅግ አሰፋሪ ነው ያሉት የፍትህ ጋዜጣ አዘጋጆች የደህንነት ኃይሎቹ በሚያደርሱብን ስቃይና ወከባ በመፍራት ሀገር ጥለን አንወጣም ሲሉም በጋዜጣቸው ላይ አቁዋማቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡

**«እውነት ይህቺ ሀገር የማን ናት?»** በሚል ተከታታይ እትማቸው ላይ ባወጡት መጣጥፍ እንደገለጹት ከሆነ የህወሀቱ ሊቀመንበር መለስ ዜናዊ ህዝቡን እያስፈራራ ለዘመናት ለመቆየት ቢያስብም

እድሉ እንደነ ሙባረክ መሆኑ አይቀሬ ነው ያሉት ጋዜጠኞቹ በደህንነት ጋጋታ ከያዝነው አቋዋም ፍጹም አንፈታም ሲሉም አቋዋማችን ለህዝብ ይፋ አድርገዋል፡፡

የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ አሳታሚ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ ከተሰደደ እና ጋዜጣው ስራ ካቆመ ወዲህ ሙሉ ለሙሉ የደህንነት ኃይሎች በፍትህ ጋዜጣ አዘጋጆች ላይ ማድረጋቸውን የገለጹት ጋዜጠኞቹ እያንዳንዱዋ እንቅስቀሴያቸው በደህንነት ቁጥጥር ስር መግባቱንና ህልውናቸውም አደጋ ላይ መውደቁን ገልጸዋል፡፡

ምናልባትም እርምጃ ሊወሰድብን ይችላል በሚል ፍርሀት አንድ ላይ መዋል እና ማደር ጀምረናል ያሉት ጋዜጠኞቹ ሌሊት በቤታችን ግድግዳ ስር እየተወሸቁ የምናወራውን እያደመጡ ሲሆን ቀን ቀን ደግሞ ዱካችንን እየተከታተሉ ምራቃቸውን ጭምር እየተፋብን ይገኛሉ ሲሉም በይፋ አጋልጠዋል፡፡በአሁኑ ሰዓት ጋዜጠኞቹ በህብረት እየኖሩ እንደሚገኙና እነ መለስ ዜናዊ የላኩዋቸውን ሰላዮች እንዲያስታግሱልን ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡